# የብልጽግና ፓርቲ

## የአባላት ምልመላ፣ ግንባታ እና ስንብት መመሪያ

## ቁጥር-----/2017

## (ለውይይት የቀረበ)

**ጥቅምት/2017 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# የብልጽግና ፓርቲ የአባላት ምልመላ፣ ግንባታ እና ስንብት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር----- /2017

አንድ ፓርቲ ጠንካራና ውጤታማ ፓርቲ ሆኖ እንዲቀጥል ከሚያስችሉ ጉዳዮች ዋነኛው በጠንካራ አባላት የተደራጀና ተቋማዊ አሰራርን በተከተለ አግባብ አባላቱን ማስተዳደር መገንባትና መምራት ሲችል በመሆኑ፣

ጠንካራ አባላትን በማደራጀት በአግባቡ ለመምራት ጠንካራ አባላት ወደ ፓርቲው የሚመጡበት፣ ለአባላት ጥንካሬ መሰረታዊ የሆኑ አቅሞች የሚገነቡበት፣ በየግዜው የፖለቲካዊ ብቃታቸው የሚጎለብትበት እንዲሁም ከፓርቲው ጋር ያላቸው ቆይታ ሲያበቃ ጤናማ የስንብት ስርአት መኖሩ ወሳኝ በመሆኑ፣

የብልጽግና ፓርቲም ጠንካራ አባላትን ወደ አባልነት በማምጣት በየግዜው አቅማቸውን በመገንባት፤ ከፓርቲው ጋር የሚለያዩ አባላቱን በአግባቡና በስርዓት ለመምራት የሚያስችለው ዝርዝር አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በፓርቲው ውስጥ ግልጽና ውጤታማ የአባላት ምልመላ፣ ፖለቲካዊ አቅም ግንባታ እና የስንብት ስርኣትን በመፍጠር ፓርቲውን የጠንካራ አባላት ባለቤት በማድረግ፣ የፖለቲካ ብቃታቸውን በየግዜው በመገንባት የፓርቲውን ውጤታማነት፣ ጥንካሬ እና ቀጣነት ለማረጋገጥ እንዲሁም አባላት ከፓርቲው ጋር በሚለያዩበት ግዜ በቀጣይ ለፓርቲው አቅም በሚሆኑበትና ጤናማ በሆነ መልኩ እንዲሰናበቱ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የብልጽግና ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 7 እና አንቀጽ 40 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## <u>ምዕራፍ አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የብልጽግና ፓርቲ የአባላት ምልመላ፣ ግንባታ እና ስንብት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር--/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ፓርቲ"** ማለት የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) ነው።
2) **"ፕሮግራም"** ማለት የብልፅግና ፓርቲ የፕሮግራም ነው።
3) **"መተዳደሪያ-ደንብ"** ማለት የብልጽግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ ማለት ነው፣
4) **"ማዕከላዊ ኮሚቴ"** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከጉባኤ እስከ ጉባኤ ፓርቲውን የሚመራ ከፍተኛ የብልጽግና ፓርቲ አካል ነው፤
5) "የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር **ኮሚሽን**" ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በየደረጃው የተቋቋመው የፓርቲው የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን ማለት ነው፤
6) **'ዋና ጽህፈት ቤት"** ማለት የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽህፈት ቤት ነው።
7) **"ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት"** ማለት ከክልል እስከ ቀበሌ ባሉ መዋቅሮች የተቋቋመ የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ነው።
8) **"ክልል"** ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል።
9) **"ዞን"** ማለት ለክልል ተጠሪ የሆኑ የዞን አስተዳደሮች፣ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች እና በዞን ደረጃ ያሉ ከተሞችን እና ልዩ ወረዳዎችን የሚያጠቃልል ነው።
10) **"ወረዳ"** ማለት በክልሎች፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የወረዳ ደረጃ የተሰጣቸው የአስተዳደር አካላትን ያጠቃልላል።
11) **"ቀበሌ"** ማለት ከወረዳ በታች ያለ የአስተዳደር እርከን ማለት ነው።

12) **“መሰረታዊ ድርጅት”** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመና ከ22 እስከ 210 አባላትን ያቀፈ የሕዋሳት ስብስብ የሆነ አደረጃጀት ማለት ነው፡፡

13) **“ሕዋስ”** ማለት ከ11 እስከ 35 አባላትን ያቀፈ ሆኖ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የአባላት የዕለት ተዕለት አቅም የሚገነባበት አደረጃጀት ነው፡፡

14) **”ኮንፈረንስ“** ማለት አባላት በየወሩ በመደበኛነት በየመሰረታዊ ድርጅታቸው በጋራ ሆነው የተግባራት አፈጻጸም ግምገማና የተለያዩ ውሳኔዎችን የሚያስተላልፉበት መድረክ ነው፡፡

15)**“ሙሉ አባል”** ማለት የዕጩነት ጊዜ የጨረሰ እና በመሰረታዊ ድርጅት የአባላት ኮንፈረንስ ወደ ሙሉ አባልነት የተሸጋገረ አባል ነው፡፡

16)**“እጩ አባል”** ማለት የደጋፊነት ጊዜ የጨረሰ እና በመሰረታዊ ድርጅት የአባላት ኮንፈረንስ ወደ ዕጩ አባልነት የተሸገረ ዕጩ አባል ነው፡፡

17)**’ደጋፊ“** ማለት የብልፅግና ፓርቲ ዓለማዎች፣ እሳቤዎች፣ መርሆዎችና እሴቶችን ተቀብሎ የሚደግፍ ግለሰብ ማለት ነው፡፡

18)**“መልካም የፓርቲ ሥነ-ምግባር”** ማለት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተደነገጉ የአባልነት ግዴታ፣ የፓርቲው መርሆዎች፣ እሴቶችና የአሰራር መርሆዎችንና የፓርቲውን ስነ-ምግባር ማክበርና በጥብቅ መፈፀም እንዲሁም ህብረተሰቡ የሚስማማባቸውን የግብረ-ገብ እሴቶችን ማክበርና መልካም ተግባራትን በመፈጸም አርአያ ሆኖ መገኘት ማለት ነው፡፡

19)**“አመራር”** ማለት የፓርቲውን ፕሮግራም ለማስፈጸም በየደረጃው ባለው የፓርቲው መዋቅሮች በሃላፊነት የተመደበ ወይም የተመረጠ ማለት ነው፡፡

20)**“የአባላት ግንባታ”** ማለት በየወቅቱ ፓርቲው ከህዋስ ውይይት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ አመራር ስልጠና የሚሰጥባቸው የአቅም ግንባታ ስራዎችን የሚያጠቃልል ነው፡፡

21) **“የአባላት ስንብት”** ማለት አባሉ ከፓርቲው ጋር የነበረው ቆይታ በተለያዩ ምክኒያቶች አብቅቶ፤ ከፓርው ጋር የሚለያይበትና ከፓርቲው የሚሰነበትበት ሂደት ነው፡፡

22)**“የክብር አባላት ”** ማለት በፓርቲው ውስጥ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተው በዕድሜ፣ ወይም በሌሎች አስገዳጅ ሁኔታዎች ወይም በፓርቲው እውቅናና ፍቃድ ከሙሉ አባልነት ወደ ክብር አባልነት ተሸጋግረው የክብር አባልነት እውቅና የሚሰጣቸው አባላት ናቸው፡፡

23)**“ብልሹ አሰራር”** ማለት ከፓርቲው እሴቶችና መርሆዎች ያፈነገጠ ተግባር ውስጥ መገኘትን የሚያለክት ነው፡፡

24)**“ግንባር ቀደም አባል”** ማለት ከአባላት መካከል በአመለካከታቸው፣ በስነ-ምግባራቸው፣ በእውቀትና ክህሎታቸው እና በተግባር አፈጻጸም ውጤታመነታቸው የላቁ ሆነው በአባላት ዘንድ እንዲሁም በአካባቢ ማህበረሰብ በአርአያነት የሚታዩ አባላት ነው፡፡

25) በዚህ መመሪያ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፣

## 3. የመመሪያው ዓላማ፤

ፓርቲው በየግዜው በጠንካራ አባላት እየተደራጀ፣ የአባላቱ ፓለቲካና የማስፈጸም ብቃት እንዲጎለብት እንዲሁም ከፓርቲው ጋር ያላቸው ቆይታ ሲያበቃ ጤናማ በሆነ መንገድ እንዲለያዩ ለማድረግ የሚያስችል ግልጽና ውጤታማ የአሰራ ስርዓት በመዘርጋት የፓርቲውን ጥንካሬ፣ ውጤታማነትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ ነው፡፡

## 4. የየአባላት ምልመላ፣ ግንባታና ስንብት መርሆዎች፤

የአባላት ምልመላ ግንባታና ስንብት ስራ በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል፡-

1) የአባላት ምልመላ፣ ግንባታና ስንብት አሰራርን የጠበቀና በትክክለኛ መረጃና ማስረጃ ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፣

2) የአባላት ምልመላ፣ ግንባታና ስንብት ስራ አሰራርን የተከተላ ግልፅ፣ ዴሞክራሲያዊና ተጠያቂነት መሰረት የደረገ መሆን ይኖርበታል፣

3) የምልመላ ስራው ጥራት በማስጠበቅ የፓርቲውን ውስጣዊ አንድነትና ውጤታማት የበለጠ ማጠናከር ይኖርበታል፣

4) የአባላት ግንባታ በሁሉም አባላትና የፓርቲው መዋቅሮች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ በሚያረጋግጥ መልኩ የግልፀኝነትና ተጠያቂነት አሰራርን ተከትሎ የሚመራ ይሆናል፣

5) የአባላት ስንብት አሰራርን ተከትሎ ጤናማ በሆነ አግባብ የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 5. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን፤

ይህ መመሪያ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲ አደረጃጀቶች፣ አመራር፣ አባላት፣ እጩ አባላት እንዲሁም የክብር አባላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል አንድ

## የአባላት ምልመላ አፈጻጸም

### 6. የአባላት ምልመላ የመመዘኛ መስፈርቶች

1) በፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (1) ስር ለፓርቲው አባልነት የሚያበቁ መመዘኛዎች ተብለው የተዘረዘሩ መመዘኛዎች የአባላት የመልመላ የመመዘኛ መስፈርቶች ናቸው።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የአባላት ምልመላ ስራው በየግዜው ፓርቲው የአባላት ምልመላን በተመለከተ በሚያስቀምጣቸው ስትራቴጂዎች መሰረት ልዩ ትኩረት በሚሹ ጉዳዮችን በመለየት የሚከናወን ይሆናል።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በተሰማራበት የስራ ዘርፍ ግንባር ቀደምና ለሌሎች አርአያ የሆነ፦
   - ሀ) አርሶ አደር፦ በፓርቲና በመንግስት በተቀመጠውን ሁሉን አቀፍ የልማት ስትራቴጂ እና አዳዲስ ኢኒሼቲቮችን ወደ ስራ በመለወጥ ምርትና ምርታማነትን መጨመር የቻለ፣ ለራስና ለሀገር እድገት ትርጉም ያለው ስራ መስራት የሚችል እና በቁጠባና ኢንቨስትመንት መሳተፍ የሚችል፤
   - ለ) አርብቶ አደር፦ በእንስሳትና በእንስሳት ተዋፅኦ ምርትና ምርታማነት ላይ ከቤተሰብ ፍጆታ አልፎ ለገበያ የሚያቀርብ ምርት ማምረት የሚችል እና በቁጠባና ኢንቨስትመንት መሳተፍ የሚችል፤
   - ሐ) ኢንተረፕራይዝ አንቀሳቃሽ፦ በጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሽነት ውጤታማ የሆነ፣ ለሌሎች አርአያ ወይም ሞዴል የሆነ በብድር አመላለስ አርአያ የሆነ እና ለተቀሩተ ስራ ፈላጊ ወጣቶች የስራ ዕድል በመፍጠር ሀገራዊ ግዴታውን የሚወጣ፤
   - መ) መንግስት ሰራተኛ፦ በተሰማራበት የመንግስት ስራ በተግባር አፈጻጸሙ ግንባር ቀደም የሆነ፣ ከብልሹ አሰራር የፀዳና ቀልጣፋ አገልግሎት ለህብረተሰቡ የሚሰጥ፤

ሠ) ባለሃብት፡- ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የባለሀብት ደረጃ የሚመደቡ ሆኖ ለሀገር እድገት አስተፅኦ በሚያደርጉ የስራ ዘርፎች የተሰማራ፣ ሃገራዊ ግዴታውን በአግባቡ የሚወጣ እና ለዜጎች የስራ እድል ፈጠራ ትልቅ ሚና ያለው፤

ረ) ላብ አደር፡- በተለያዩ ኢንደስትሪዎች ውጥ የተሰማራ፤ ለኢንደስተሪዎች ውጤታማነት እንዲሁም በኢንደስተሪ አካባቢ ጤናማ የስራ ምህዳር እንዲፈጠር በሚሰሩ ስራዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ የሆነ፤

ሰ) ተማሪ፡- በትምህርቱ ግንባር ቀደም የሆነ፣ ሌሎች ተማሪዎችን በመርዳትና በማገዝ የሚታወቅ፣ በመልካም ሥነ-ምግባር የተመሰከረለት እና በትምህርት ቤትና በመኖሪያ አከባቢ በተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች ንቁ ተሳታፊ የሆነ፤

4) ማንኛውም በፓርቲ አባልነት የሚመለመል ሰው ዕድሜው ከ65 ዓመት በላይ መሆን የለበትም፡፡

## 7. <u>የፓርቲ አባላት ምልመላ መንገዶች</u>

ግለሰቦች ወደ ፓርቲው አባልነት በሁለት መንገድ ሊመጡ ይችላሉ፡፡ እነርሱም፡-

1) በፓርቲ አካላት፣ አመራርና አባላት አማካይነት በሚደረግ ምልመላ ወይም
2) በግለሰቡ ፍለጎት በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት የሚደረግ ምልመላ ናቸው፡፡

## 8. <u>በፓርቲ አካላት አማካይነት የሚደረግ የምልመላ ሂደት</u>

1) የአዳዲስ አባላት ምልመላ በህዋሳትና በህዋሳቱ ውስጥ በታቀፉ አባላት አማካኝነት በእቅድ ላይ ተመስረቶ መከናወን ይኖርበታል፤
2) ጠንካራ ግለሰቦችን በመለየት ወደ አባልነት የማምጠት ስራ የአባላት ተልዕኮ ሲሆን ከህዋስ አመራሮች ጋር ተቀናጅቶ የሚከናወን ይሆናል፤
3) አንድ አባል በፓርቲው ተደራጅቶ በሚንቀሳቀስበት የመኖሪያ ወይም የስራ አካባቢ ካሉ ግለሰቦች ውስጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሰረት የአባላት ምልመላ የመመዘኛ መስፈርቶችን የሚያሟሉትን የመለየት ተግባር በእቅዱ መሰረት ያከናውናል፤
4) ከላይ በንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት የተለዩ ግለሰቦች ሙሉ መረጃ ለህዋሷ አደረጃጃት ሀላፊ ይቀርባል፤
5) የህዋሷ አደረጃጀት ሃላፊ ተለይተው የቀረቡለትን መረጃዎች መርምሮ በማደራጀት በህዋስ አመራሮች መደበኛ ስብሰባ ላይ ያቀርባል፤

6) የህዋስ አመራሮች የቀረበላቸውን የተደራጀ የግለሰቦች መረጃ መርምረው በፓርቲው የውሳኔ አሰጣጥ መርህ የግለሰቦቹን የምልመላ ሂደት እንዲቀጥል ወይም እንዲቋረጥ ይወስናሉ፤

7) የአባልነት ምልመላው እንዲቀጥል ውሳኔ የተሰጠባቸው ግለሰቦችን ቀጣይ የማሰማን ስራ በውጤታማነት ሊፈጽም ለሚችል አባል ወይም አባላት ትልዕኮ በህዋሷ አማካኝነት በመስጠት ስራው እንዲሰራ ይደረጋል፤

8) የአባልነት ምልመላ ሂደቱ እንዲቋረጥ የተወሰነ ግልሰብን በተመለከተ ልየታውን ላከናወነው አባል ከነሙሉ ምክኒያቱ ተገልጾለት የምልመላ ሂደቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡

## 9. ለአባልነት የተለዩ ግለሰቦች ወደ አባልነት የማምጣት ሂደት

1) ተግባሩን እንዲፈጽም ተልእኮ የተሰጠው አካል በቂ የቅደመ ዝግጅት በማድረግ ወደ ስራው መግባት ይኖርበታል፤
2) የራሱን አመቺ ሁኔታ በመፍጠር ስለፓርቲው አጠቃላይ ፕሮግራምና ግቦች ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማያያዝ የማስገንዘብ፣ የማስረዳትና የማሳወቅ ስራን በበቂ ሁኔታ ማከናወን ይኖርበታል፤
3) በተጨማሪም ግልጽነት የሚሹ ጉደዮች ካሉ በመለየት ግጽነት እንዲፈጠርባቸው ማደረግ ይጠበቅበታል፤
4) እንደየ ግለሰቦች ባህሪና ሁኔታ ለስራው በቂ ግዜን ወስዶ የተፈጠረውን መነሳሰትና ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት በግሉ በመገምገም ወደ ፓርቲው እንዲቀላቀሉ ጥያቄ ያቀርብላቸዋል፤
5) በጥያቄው መሰረት፡-
   ሀ) ሙሉ በሙሉ ፍቀደኛ ሆነው በፓርቲው ውስጥ ገብተው ለመታገል ዝግጁ የሆኑት የእጩ አባልነት ቅጽ በመሙላት የምልመላውን ሂደት እንዲቀጥሉ ይደረጋል፣
   ለ) የፓርቲውን ፕሮግራምና አላማ የሚቀበሉ ነገር ግን በተለያዩ ምክኒያቶች ሙሉ ተሳትፎ ማድረግ የማይችሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ እና በደጋፊነት ከፓርው ጋር ለመቀጠል ዝግጁ ከሆኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 መሰረት በደጋፊ አደረጃጀት ውስጥ እንዲያዙ በማድረግ በደጋፊ አባልነት እንዲቀጥሉ ይደረጋል፣

ሐ) የፓርቲውን ፕሮግራምና አላማ የማይቀበሉ ወይም በአጠቃላይ የየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል ሆነው በፖለቲካ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ የማፈልጉ ወይም በሌሎች ምክኒያቶች የቀረበላቸውን ጥያቄ ያልተቀበሉ ውሳኔያቸውን በማክበር እና በማመስገን ከክትትል ውጪ ተደርገው ወሳኔያቸው ለህዋስ ሪፖርት ይደረጋል፡፡

10.<u>የደጋፊ አባል አመላመል</u>

1) ማንኛውም ለፓርቲ አባልነት የሚታሰብ ግለሰብ በሚኖርበት አከባቢ ወይም በስራ ቦታው በሚያሳየው ተግባራዊ ተሳትፎ የፓርቲን ዓላማ የሚደግፍ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡
2) በዚህ መሰረት ግለሰቡ በመኖሪያ ወይም በስራ ቦታው ፓርቲዉን በእዉቀት፣ በገንዘብና በጉልበት እንዲሁም ፓርቲው በሚያከናውናቸው ልዩ ልዩ ተግባራት የነቀ ተሳትፎ በፈቃደኝነት የሚያደርግ ስለመሆኑ በአባላት ቅርብ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) በሚኖርበት ወይም በሚሰራበት አካባቢ ደጋፊ ለመሆን ፍቃደኝነቱ የተረጋገጠ ግለሰብ ከሚቀራረቡትና ከሚስማሙት ሰዎች ጋር በደጋፊዎች ቡድን አደረጃጀት መታቀፍ ይኖርባቸዋል፡፡
4) የደጋፊዎች ቡድን አደራጃጀት የደጋፊው የቡድን አባላት በተመረጠ አባል የሚመራ ይሆናል፡፡
5) የደጋፊዎች ቡድን አደራጃጀት በፓርቲ ህዋስ ስር የሚደረጅ ሆኖ፣ በህዋሱ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ የሚደረግለት ይሆናል፡፡

11. <u>በግለሰቡ ፍለጎት በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት የሚደረግ ምልመላ</u>

1) በፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (1) ስር ለፓርቲው አባልነት የሚያበቁ መመዘኛዎች ተብለው የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ግለሰብ በግል ፍላጎቱ መሰረት አባል ለመሆን ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡
2) ግለሰቡ ጥያቄውን በጽሁፍ በመኖሪያ ወይም በስራ አካባቢው ለሚገኝ የፓርቲው ህዋስ ማቅረብ ይችላል፡፡

12.<u>ስለማጣራት</u>

1) የህዋስ አመራር ኮሚቴ በቀረበው ማመልከቻና የተሞለው ቅጽ መነሻነት ለዕጩ አባልነት የቀረበ ማመልከቻ ግለሰቦችን በመኖሪያ ወይም በስራ ቦታቸው ማጣራት ያደርጋል፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት አስፈላጊውን ማጣራት ተደርጎ የተረጋገጠ ግለሰብ፤ የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብና የዲሲፕሊን መመሪያ ላይ ግንዛቤ ይዞ ስለመቀበሉ እና በጽናት ተግባራዊ ለማድረግ ፍቃደኛ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

## 13.እጩ አባልነት ስለማጽደቅ

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሰረት የፓርቲ አባል መመልመያ መስፈርቶች መሟላታቸው የተረጋገጡትንና በፓርቲውን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ላይ ግንዛቤ ተፈጥሮላቸው ወይም በግል ስለ ፓርቲው መልካም እሳቤ ስለመያዛቸው የተረጋገጡትን ከግለሰቡ የዕጩ አባልነት ማመልከቻና የተሞለው ቅጽ ጋር የራሱን የውሳኔ ሀሳብ ለህዋስ ጠቅላላ ስብሳባ አቅርቦ ለእጩ አባልነት ብቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ ለመሰረታዊ ድርጅት ቀርቦ እንዲጸድቅ ያስወስናል፤

2) በህዋስ ተቀባይነት ካገኘ ከህዋስ ጠቅላላ ስብሰባ ውሳኔ ጋር ማስረጃዎችን አደራጅቶ ለመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ለውሳኔ ያቀርባል፤

3) የመሠረታዊ ድርጅት የአደረጃጀት ንዑስ ኮሚቴ ከህዋስ የቀረቡለትን የእጩ አባልነት የይጽደቅ ውሳኔ በትክክል መስፈርቱን አሟልተው የቀረቡ መሆናቸውን ለመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ለተጨማሪ ማጣራት ያቀርባል፤

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) መሰረት በመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ተቀባይነት ካገኘ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለመሰረታዊ ድርጅት የአባላት ኮንፈረንስ ያቀርባል፤

5) የመሰረታዊ ድርጅት የአባላት ኮንፈረንስ የመሠረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳብ ካደመጠ በኃላ ግለሰቡን በዕጩ አባልነት ለመቀበል ወይም ላለመቀበል አንድ በአንድ ድምፅ በመስጠት ይወስናል፡፡

## 14..ውሳኔ ስለማሳወቅ

1) በመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ የዕጩ አባልነት የጸደቀላቸውን ዕጩ አባላት ዝርዝር ጥያቄ ላቀረበው ህዋስ እና ለወረዳ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሙሉ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

2) ዕጩ አባልነቱ የጸደቀለት ግለሰብ በመሰረታዊ ድርጅት የአደረጃጀት ንዑስ ኮሚቴ የግል ማህደር ተከፍቶላት ውሳኔው እንዲሰፍርና እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

3) እጩ አባልነት የጸደቀላቸው ግለሰቦች ዝርዝር መረጃ ለዚሁ የተዘጋጀ የመረጃ ቋት ካለ ሙሉ በሙሉ እንዲያስገቡ ይደረጋል፡፡

## 15. <u>የዕጩ አባልነት ጊዜ አቆጣጠር</u>

የዕጩ አባልነት ጊዜ የሚታሰበው በመሠረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ ዕጩ አባል እንዲሆን ከጸደቀበት ጊዜ ይጀምራል፡፡

## 16. <u>ቃለ መሃላ ስለመጸም</u>

1) ዕጩ አባልነቱ የጸደቀለት ግለሰብ ወይም ግለሰቦች በመሠረታዊ ድርጅት የአባላት ኮንፈረንስ ፊት ቃለ መሃላ ይፈጽማሉ፡፡

2) የቃለ መሃላ ይዘቱም የሚከተለው ይሆናል፡፡

> "እኔ ________________ በዛሬው ዕለት የብልፅግና ፓርቲ ዕጩ አባል ሲሆን የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብና የዲሲፕሊን እና ሌሎች መመሪያዎች ተቀብዬ ለማክበር፣ ለማስከበርና የሚጠበቅብኝን ግዴታዎች በታማኝነት ለመፈጸም ቃል እገባለሁ፡፡"

## 17. <u>የእጩ አባላት መብትና ግዴታ</u>

1) አንድ እጩ አባል እጩ አባልነቱ በመሠረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 11 ንኡስ አንቀጽ 2 የተገለጹ መብቶች ይኖሩታል፡፡

2) አንድ እጩ አባል እጩ አባልነቱ በመሠረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12 ስር የተደነገጉ ግዴታዎች ይኖሩበታል፡፡

## 18.<u>እጩ አባላትን ማብቃት፣ የክትትልና ድጋፍ ሂደት</u>

1) የእጩ አባልነት ቅጽ የሞሉ እጩ አባለትን የማብቃት፣ የመደገፍና የመከታተል ተግባር በህዋሰት አመራሮች አማካኝነት ታቅዶ ፈጻሚ አካል ተመድቦለት መከናወን ይኖርበታል፤
2) አንድ እጩ አባል የሙከራ ግዜ ከስድስት ወር እስከ ዘጠኝ ወር የሚቆይ ይሆናል፤
3) አንድ እጩ አባል በተዘረጋለት መርሃግብር አማካኝነት በፓርቲው ፕሮግራምና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ በቂ እውቀትና ግንዛቤ መያዝ ይኖረበታል፤
4) በፓርቲው ፕሮግራምና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ በቂ እውቀትና ግንዛቤ ለማስያዝ፡-
   ሀ) ማንበብና መጽሃፍ ለሚችሉ እጩ አባላት ሰነዶቹ ተሰጥቷቸው አንብበው እንዲረዱና በተረዱት ላይ የውይይት መድረክ ተዘጋጅቶላቸው እንዲበቁ ይደረጋል፣
   ለ) ማንበብና መጽሃፍ ለማይችሉት በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ ገለጻ ተዘጋጅቶላቸው ግንዛቤ እንዲይዙ ከተደረገ በኂላ ግንዛቤያቸውን በውይይት እንዲያዳብሩት ይደረጋል፤
5) በፓርቲው ፕሮግራምና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ በቂ እውቀትና ግንዛቤ መያዝ ያለመያዙ ለማረጋገጥ ከፓርቲው በመዕከል ወይም በፓርቲ ዋና /ጽ/ቤት በሚቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በየደረጃው በሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች በሚዘጋጅ የቃል ወይም የጽሁፍ ምዘና አማካኝነት ይረጋገጣል፤
6) በፈተናው መሰረት፡-
   ሀ) ያለፈ እንደሆነ በሂደቱ የሚቀጥል ሲሆን፣
   ለ) ከወደቀ በድጋሜ መርሃግብር ተዘጋጅቶለት ለሁለተኛ ግዜ እንዲፈተን ይደረጋል፣
   ሐ) በድጋሜ ፈተናው ያለፈ እንደሆነ በሂደቱ የሚቀጥል ሲሆን ያላለፈ እንደሆነ ግን ለአባልነት ብቁ እንዳልሆነ ተወስዶ የክትትል ሂደቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል፤
7) በፓርቲው ፕሮግራምና መተዳደሪ ደንብ ላይ ባገኘው እውቀትና ግንዛቤ ሙሉ በሙሉ እምነት ያለውና ለተግባራዊነቱም ቁጠኛ መሆኑን ቃሉን መስጠት እና በተግባርም ማረጋገጥ ይኖረበታል፤
8) እጩ አባሉ በቆይታ ግዜው ከህዋሷ የሚሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ መፈጽም ይኖርበታል፤
9) እጩ አባሉ በስድት ወራት በተደረገለት ድጋፍና ክትትል እንዲሁም በተሰጠው ተልዕኮ ውጤታማነቱን የህዋስ አመራሮች የሚገመግሙ ይሆናል፤

10) በግምገማው እጩ አባሉ ውጤታማነቱ ከተረጋገጥ ወደ ሙሉ አባልነት እንዲመጣ ለመሰረታዊ ድርጅት አመራሮች ጥያቄው ይላካል፤

11) በግምገማው እጩ አባሉ ውጤታማ እንዳልነበረ ከተረጋገጥ ተጫማሪ የሙከራ ሶስት ወራት ተሰጥቶት ድጋፍና ክትትል ተደርጎለት እንዲበቃ ይደረገጋል፤

12) በተጨማሪው ሶስት ወራት ውጤታማ ከሆነ ወደ ሙሉ አባልነት እንዲመጣ ለመሰረታዊ ድርጅት አመራሮች ጥያቄው ይላካል፤

13) ይሁንና በተጨማሪው ሶስት ወራትም ውጤታማ ያልሆነ እጩ አባል ያለበት ችግር ተገልጾለት ከእጩ አባልነት እንዲሰረዝ ተደርጎ ክትትሉ ይቋረጣል፡፡

## 19. <u>የሙሉ አባልነት የማጽደቅ አፈጻጸም</u>

1) ዕጩ አባሉ የዕጩነት ጊዜውን እንደጨረሰ የህዋሷ አመራሮች የድጋፍና ክትትል እና የፈተና ውጤቱን የማጣራት ስራ ይሰራሉ፤

2) በእጩ አባሉ ላይ ሲደረግ የነበረው ክትትልና ድጋፍ እንዲሁም እውቀትና ግንዛቤውን ለመለካት የተሰጠው ፈተና ውጤት ለሙሉ አባልነት የሚያበቃው መሆኑ ከተረጋገጠ የታቀፈበት ህዋስ አመራር ሙሉ አባልነቱ እንዲጸድቅ ለመህዋሷ ያቀርባሉ፡፡

## 20.<u>ውሳኔ አሰጣጥ</u>

1) የህዋስ ጠቅላላ አባላት ከህዋስ አመራር ኮሚቴ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ካደመጠ በኃላ ይወስናል፡፡

2) በህዋስ ጠቅላላ አባላት ሙሉ አባል እንዲሆኑ ይሁንታ ያገኙ ዕጩ አባላት ዝርዝር ለመሠረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ከሪፖርት ጋር ይቀርባል፣

3) የመሠረታዊ ድርጅት አደረጃጀት ንዑስ ኮሚቴ ከህዋስ አመራር ኮሚቴ የሙሉ አባልነት እንዲጸድቅላቸው የቀረቡትን ተጨማሪ ማጣራት አደርጎ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ቀርቦ ይወሰናል፣

4) የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ የውሳኔ ሀሳብ ለመሰረታዊ ድርጅት የአባላት ኮንፈረንስ ቀርቦ አንድ በአንድ ውይይት ከተደረገበት በኃላ ዕጩ አባሉ ወደ ሙሉ አባልነት እንዲሸጋገር ወይም የዕጩነት የቆይታው ጊዜ ለሶስት ወር እንዲራዘም ወይም ከዕጩ አባልነት እንዲሰረዝ ድምጽ በመስጠት ይወስናል፣

## 21. ውሳኔ ስለማሳወቅ

1) የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ የሙሉ አባልነት የጸደቀላቸውንና የዕጩነት የቆይታው ጊዜ ለሶስት ወር የተራዘመላቸውን እንዲሁም ከዕጩ አባልነት እንዲሰረዙ የተወሰኑትን ዝርዝር ከውሳኔ ጋር ጥያቄ ላቀረበው ህዋስ እና ለወረዳ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሙሉ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

2) ውሳኔው የተገለጸላቸው የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤቶች የአባሉን ሙሉ መረጃ ወደ መረጃ ቋት ያስገባሉ፡፡

3) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (4) የተወሰነው ውሳኔ በህዋስ ጠቅላላ አባላት በተገኙበት ውሳኔው ልገለጽላቸው ይገባል፡፡

## 22. የሙሉ አባልነት ጊዜ አቆጣጠር

1) የሙሉ አባልነት ጊዜ የሚታሰበው በመሠረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ ሙሉ አባል እንዲሆን ከጸደቀበት ጊዜ ይጀምራል፡፡

## 23.የሙሉ አባላት መብትና ግዴታ

1) አንድ ሙሉ አባል ሙሉ አባልነቱ በመሠረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 11 ንኡስ አንቀጽ 1 የተገለጹ መብቶች ይኖሩታል፡፡
2) አንድ ሙሉ አባል ሙሉ አባልነቱ በመሠረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12 ስር የተደነገጉ ግዴታዎች ይኖሩበታል፡፡

## 24. በአባላት ምልመላ ሂደት የባለድርሻ አካለት ተግባርና ኃላፊነት

1) ዋና ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት
   ሀ) በፓርቲው ውስጥ የሚከናወኑ የአባላት ምልመላን በየግዜው እየገመገመ የአባላት ምልመላ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ እንዲተገበሩ ያደርጋል፡፡
   ለ) እጩ አባላት በሚደረግላቸው የድጋፍና ክትትል በፓርቲው ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ላይ በቂ እውቀትና ግንዛቤ መያዛቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የምዘና ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲደረግ ያደርጋል፡፡
2) በየደረጃው ያሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) የአባላት ምልመላን ስራ በዋና ጽ/ቤት በሚቀመጥ ስትራቴጂ መሰረት በእቅድ ተይዞ በሚፈለገው ደረጃ በጥራትና በውጤታማነት እንዲከናወን የድጋፍና ክትትል ስርኣት ዘርግተው ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

ለ) የሙሉ አባላት መረጃ ተደራጅቶ ወደ አባላት መረጃ ቋት እንዲገባ በማድረግ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋሉ፡፡

3) የመሰረታዊ ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) የአባላት ምልመላ ስራ በእቅድ ላይ ተመስረቶ እንዲሰራ ለህዋሳት አቅጣጫ በማስቀመጥ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል

ለ) ከህዋሳት የእጩ አባልነት ግዜያቸውን በውጤታማነት ጨርሰው ሙሉ አባል እንዲሆኑ የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች መርምሮ ይወስናል፡፡

4) የህዋሳት ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) ህዋሳት በሚንቀሳቀሱበት አካባቢ የአባላት ምልመላን ስራ በማቀድ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፤

ለ) የአደዲስ አባላት ምልመላ ስራ በእቅዱ መሰረት በአባለት ታቅዶ እንዲፈጸም የክትትልና ድጋፍ ስርኣት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋሉ፤

ሐ) በአባላት ተለይተው የቀረቡ ጠንካራ ግላሰቦች በህዋስ አመራር ተገምግመው ወደ ቀጣይ የምልመላ ሂደት እንዲኬድ ወይም እንዲቋረጥ ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጋሉ፤

መ) በምልመላ ሂደት ውስጥ እንዲገቡ የተለዩ ግለሰቦችን የማነሳሳትና የማሳመን ስራ የሚሰሩ አካላትን በመመደብ አፈጻጸመቸውን ይከታተላሉ፤

ሠ) በህዋሳት አማካኝነት እንዲሁም በግል ፍቀዳቸው የእጩ አባልነት ቅጽ ሞልተው እጩ አባል ለሆኑ እጩ አባላት የማብቃት፣ የድጋፍና ክትትል ስርዓት በመዘርጋት አፈጻጸሙን ይከታተላሉ፤

ረ) በሂደቱ ውጤታማ የሆኑትን በመለየት ለመሰረታዊ ድርጅት አመራር በማሳወቅ ወደ ሙሉ አባልነት የሚመጡበትን አግባብ ይፈጥራሉ፤

ሰ) በሂደቱ ውጤታማ ያልሆኑትን ደግሞ ምክኒያቱን በማሳወቅ ከእጩ አባልነት እንዲሰረዙ ያያርጋሉ፡፡

5) የአባላት ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) አንድ አባል በሚንቀሳቀስበት አካባቢ ጠንካራ ግለሰቦች ወደ ፓርቲው እንዲመጡ አቅዶ መስራት ይኖርበታል፤

ለ) በእቅዱ መሰረት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተቀመጡ የመመዘኛ መስፈርቶች መሰረት በማድረግ የለያቸውን ግለሰቦች ትክክለኛ መረጃ ለህዋሷ አደረጃጀት ሃላፊ ማቅረብ ይኖረበታል፤

ሐ) በቀረበው መረጃ የህዋስ አመራሮች በሚሰጡት ውሳኔ መሰረት ግለሰቡን የማሳመን ተልዕኮ የሚሰጠው ከሆነ ተልዕኮውን በቁርጠኝነት በመወጣት የደረሰበትን አፈጻጸም ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፤

መ) የእጩ አባላትን ከማብቃት፣ ከመደገፍ እና ከመከታተል አኳያ በግልም ሆነ በቡደን የሚሰጡትን ተልዕኮዎች በሚገባ መፈጸምና በየግዜው የአፈጻጸም ሁኔታውን ማቅረብ ይኖረበታል፤

ሠ) ሌሎች ተጨማሪ ከአባለት ምልመላ ጋር ተያይዘው የሚሰጡትን ተግባራት ማከናወን ይኖርበታል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የአባላት አቅም ግንባታ አፈጻጸም

### 25.የአቅም ግንባታ ፍላጎትና ክፍተት ስለመለየት

1) ማንኛውም ለአባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና ከመሰጠቱ በፊት የፍላጎትና የክፍተት ዳሰሳ ጥናት መከናወን ይኖርበታል፤
2) የአባላት ክፍተት ዳሰሳ ጥናት በየዓመቱ በጥናትና ምርምር እና በፖለቲካና አቅም ግንባታ ዘርፍ አማካኝነት በጋራ የሚከናወን ይሆናል፤
3) የዳሰሳ ጥናት የሚከናወነው ፓርቲው ከአባላት ከሚጠበቀው ሚና እና አባላት ላይ ከሚታየው የእውቀትና የአመለካከት ክፍተት አንጻር ይሆናል፤
4) የአባላት እውቀትና አመለካከት ክፍተትን በመለየት ሂደት የፓርቲው ዋና ቅ/ጽ/ቤት የሚገኙ የስራ ዘርፎች በጋራ ተሳታፊ የመሆን ግዴታ አለባቸው፤
5) የፓርቲው ፍላጎትና ክፍተት ጥናት ሳይደረግ አጫጭርም ይሁን ረጅም ስልጠና መሰጠት የለበትም፤
6) ለፓርቲው አባላት የግንባታ ሰነድ የሚዘጋጀው የክፍተትና ፍላጎት ልየታ ዳሰሳ ጥናትን መሰረት በማድረግ ብቻ ይሆናል፡፡

### 26.የአባላት ግንባታ ሰነድ ይዘትና ዝግጅት

1) የአባላት ግንባታ አካሄድ የታቀደና የታለመ እንዲሆን የስርዓተ ስልጠና ማንዋል በማዘጋጀት የሚመራ መሆን ይኖርበታል፤
2) ወደ ፓርቲው የሚቀላቀሉ ለአዳዲስ አባላት ግንባታ የሚያገለግል የፓርቲው መሰረታዊ እሰሳቤዎችና አቋሞች ላይ ግንዛቤ የሚያስጨበጥ የስልጠና ሰነዶች በዋና ጽ/ቤት አማካኝነት ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ይሆናል፡፡
3) የስርዓተ ስልጠናው ርዕሶችና ይዘቶች ከፓርቲው ዓላማዎች፣ ፓርቲው ሊደርስበት ከሚፈልገው ግብ እና ከአባላት የብቃት ክፍተት ትንተና መነሻ የሚመነጭ መሆን ይኖርበታል፤
4) የስልጠና ሰነዶች ይዘት ትኩረት የመደመር መንገድ፣ የብልጽግና ርዕዮተዓለም ንድፈ ሀሳብ፣ የብልጽግና አጠቃላይ እሳቤዎችን፣ የአባላት ዲስፕሊንና ስነምግባር እንዲሁም የፓርቲውን ፕሮግራም በሚያሰርጽ መልኩ መሆን አለበት፤
5) የሰነዶች ይዘቶች ሀገራዊ ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ብልጽግና አፈጻጸሞች፣ ተግዳሮቶች እና አፈታታቸው ላይ የተሟላ መረጃና ግንዛቤ የሚስጨብጥ መሆን አለበት፤
6) ለአባላት የሚዘጋጁ የስልጠና ሰነዶች ወቅታዊ ቀጠናዊ፣ አህጉራዊ እና አለማአቀፋዊ ሁኔታዎችን የሚተነትን ጭብጦችን የሚያካትት እንዲሆን ይደረጋል፤
7) የልሳነ ብልጽግና መጽሄት የአባላት ግንባታ አንዱና ዋነኛ የግንባታ ይዘት ምንጭ ይሆናል፤
8) የፓርቲው ከፍተኛ ተቋም (ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈጻሚ) ውይይቶችና ውሳኔዎች ላይ ግልጽነት ለመፍጠር፣ መረጃ ለአባላት ለመስጠትና በውሳኔዎች ላይ ተግባቦት ለመፍጠር የግንባታ ሰነድ ይዘት ይሆናል፤

## 27. <u>የአባላት የግንባታ ቴክኒኮች እና ዘዴዎች</u>

የብልጽግና ፓርቲ በየደረጃዉ ያሉ መዋቅሮች እነዚህን የአባላት ግንባታ ዘዴዎችና ቴክኒኮች እንደየአስፈላጊነቱ በመጠቀም አባላትን የሚገነቡ ይሆናል፡፡

1) አጫጭር መደበኛ ስልጠናዎች እና ግምገማ ነክ ስልጠናዎች የአባላት ግንባታ ዘዴዎች ተደርገው ጥቅም ላይ ይውላሉ፤
2) ወርሃዊ የህዋስ ውይይት እና የመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ መድረኮች የአባላት የአቅም ግንባታ ዘዴዎች ናቸው፡፡

3) ፓርቲው የሚያከብራቸው ልዩ ልዩ በዓላትና ስነ-ስርዓቶች ላይ የሚቀርቡ ሴሚናሮችና ወርክሾፖች ለአባላት አቅም መገንባያ መሳሪያ ተደርገው ያገለግላሉ፤
4) የፓርቲው ዌብሳይቶች፣ በዌብሳይቶች የሚለቀቁ መረጃዎች፣ የፓርቲው ሶሻል ሚዲያዎች የአባላት አቅም ግንባታ ቴክኒኮች ሆነው ያገለግላሉ፤
5) አባላት ራስን የማብቃት እቅድ በማዘጋጀት በንባብ፣ ከሌሎች ጋር ኢ- መደበኛ የሆነ ውይይት ማድረግ፣ የተግባር ተልዕኮ፣ ራሳቸውን ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚገነቡበት የግንባታ ቴክኒኮች ናቸው፡፡
6) አመራሩ ከእርሱ ከፍ ያለ የአመራር ደረጃ ላይ ካለ አመራር ልምድና ምክር እንዲያገኝ የማድረግ ግንባታ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላል፣
7) በልዩ ልዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ብሄር ብሄረሰብ አባላትን የርስ በርስ ግንኙነትና የባህል ትውውቅ መርሃ ግብሮችን በማዘጋጀት የፓርቲውን የወንድማማችነትና እህትማማችነት እሴትና ባህል የማጎልበት ቴክኒክ ጥቅም ላይ ይውላል፤
8) የአባላት መደበኛ ግምገማዎችና ምዘናዎችን በመጠቀም የአመለካከት ግንባታ ማከናወኛ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላል፤
9) ፓርቲው በሲኒየር አመራርና ፖለቲከኞች ለተኪና ኮር አመራሮች የምክርና ድጋፍ (ሜንተሪንግና ኮቺንግ) የግንባታ ዘዴ ተግባር ላይ የሚያውል ይሆናል፤
10)በፓርቲው አመራር፣ አባላትና ህዝብ ተሳትፎ የተከናወኑ የልማት ስራዎች በማስጎብኘት እንዲሁም የተሻለ አፈፃፀም ካስመዘገቡ፣ ተቋማትና አካባቢዎች ልምድና ተሞክሮ እንዲወስዱ በማድረግ አቅማቸው የሚገነባ ይሆናል፤

## 28. <u>የፓርቲው እና የአባላት መብትና ኃላፊነት</u>

1) የአባላት መብቶች

ሀ) ሁሉም አባላት በአመት አንድ ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጠውን የአመለካከት፣ የንድፈ ሀሳብ እውቀት እና የክህሎት መደበኛ ስልጠናዎች እድል የማግኘት መብት አለው፤

ለ) አባላት ወቅታዊ ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ፣ ቀጣናዊ እና ሀገራዊ ሁኔታዎችን መሰረት ያደረጉ፣ የአስተሳሰብና የተግባር አንድነት የሚገነቡ እና ለወቅታዊ ተልዕኮ የሚያዘጋጁ ስልጠናዎችን እድል ያገኛሉ፤

ሐ) ሁሉም አባል በሚዘጋጀው የግንባታ መድረኮች በአካል የመገኘትና ሀሳብ በመስጠት በንቃት በመሳታፍ የፖለቲካ አቅሙን የመገንባት መብት አለው፤

መ) በህዋስና በመሰረታዊ ድርጅት መድረኮች አባላት ሀሳብን በነጻነት የማራመድ፣ ስለራሱ፣ ስለአካል፣ ስለፓርቲው ማወቅ የሚገባውን ነገር የመጠየቅና መልስ የማግኘት መብት አለው፤

ሠ) የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና ዕቅዶችን የማወቅ እና ለተግባራዊነታቸው በግንባር ቀደምትነት የመታገል መብት አለው፤

ረ) በፓርቲው ጉባኤዎች የመሳተፍ፣ በውይይት የመካፈልና በማንኛውም ጉዳይ ላይ በሕጋዊ መድረኮች ሐሳቡን የማቅረብና የመማር መብት አለው፤

ሰ) ማንኛውም የፓርቲው ደጋፊ የሆነ ሰው በእጩ አባልነት ወደ ፓርቲው የመቀላለቀልና ከተቀላቀለበት ጊዜ ጀምሮ በህዋስ በመሳተፍ ፖለቲካዊ አቅሙን የመገንባት መብት አለው።

2) የአባላት ግዴታዎች

ሀ) ማንኛውም አባል በሚዘጋጀው የግንባታ መድረኮች የመሳታፍና የፖለቲካ አቅሙን የመገንባት ግዴታ አለበት፤

ለ) አባላት በሚዘጋጅላው ወርሃዊ የህዋስ ውይይት እና በኮንፈረንስ መድረኮች የመሳተፍ፣ በአካል በመገኘት እና ሀሳብ በመስጠትና በመማማር ንቁ ተሳትፎ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፣

ሐ) ሶስት ጊዜ በተከታታይ የህዋስ መድረኮች ያልተገኘ አባል፣ የአባላት ዲስፕሊን መመሪያ በሚደነግገው መሰረት እርምጃ የሚወሰድበት ይሆናል፤

መ) ለግንባታ የሚያስፈልጉ የልሳነ ብልጽግና መጽሄት ህትመት፣ ጋዜጦች እና ሌሎች የግንባታ የህትመት ጽሁፎች ወጪ አባሉ በግል የመሸፍን ግዴታ አለበት፣

ሠ) አባላት ያለፓርቲው እውቅናና ፍቃድ በሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች መድረክ መሳተፍ የለባቸውም፤

## 29.<u>የፓርቲው መዋቅሮች ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) ፓርቲው ለአባላት ግንባታ የሚያገለግሉ አስፈላጊውን ሎጂስቲኮችን፣ የግንባታ ቦታዎችንና ፋሲሊቲዋችን የማመቻቸት ኃላፊነት አለባቸው።
2) ለህዋሳትና መሰረታዊ ድርጅት ውይይት መድረክ በየመዋቅሩ የሚገኙ የፓርቲ ቅ/ጽቤቶች ያመቻቻሉ፣

3) ሁሉም መዋቅሮች የአባላት ግንባታ እቅድ፣ ክትትልና ግብረ-መልስ አሰጣጠ ስርኣት የሚዘረጉ ይሆናል፤

4) ሁሉም መዋቅሮች ለአባላት መደበኛና ወቅታዊ ተልዕኮዎችን በመስጠት የማስተባበር ልምድ፣ ቁርጠኝነት፣ ተግባራዊ የአመራር ክህሎት እና ሁሉን አቀፍ የአመራር ብቃት እንዲያዳብሩ ዕድሎችን ያመቻቻል፤

5) ስትራቴጂክ የሥራ አመራር ዘርፍ በየግማሽ ዓመቱ ወይም በዓመቱ የሚያደረገውን የፓርቲው ሥራዎች ሱፐርቪዥን መሰረት በማድረግ የክፍተት ልየታ በማከናወን ለአቅም ግንባታ ዘርፍ የሚያቀርብ ይሆናል።

6) የአደረጃጀት ዘርፍ የአባላት ምዘናና ግምገማን መሰረት በማድረግ የክፍተት ልየታ በማድረግ የሚያቀርብ ይሆናል።

7) ክልሎች የስልጠና ፍላጎት በመለየት ክፍተቶቹን ለመሙላት የተመረጡትን የሥልጠና አይነቶችን መረጃ ለዋና ጽ/ቤት ፖለቲካና አቅም ግንባታ ዘርፍ መላክ ይኖርባቸዋል።

8) የፖለቲካና አቅም ግንባታ ዘርፍ ከክልሎች የተላኩለትን የተለዩ ክፍተቶችና የያዘ መረጃ በማጠናቀር ሀገራዊ የስልጠና ዕቅድና መርሃ-ግብር ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፤

## 30. የአባላት ግንባታ ውጤታማነት ስለማረጋገጥ

1) የአባላት ግንባታ ስራዎች ውጤታማነት በየአመቱ በሚደረግ ዳሰሳ ጥናት፣ የአባለላት ምዘናና እና በፓርቲ በሚደረግ ሱፐርቪዥን የሚረጋገጥ ይሆናል።

2) የግንባታ ውጤታማነት የሚረጋገጠው የፓርቲው ዓላማ መሰካቱን በሚያመላክት በፓርቲው ስታረቴጂክ ስራ አመራር በተዘጋጀ ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካች ይሆናል።

3) የብልጽግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት በየአመቱ የአባላት ግንባታ አፈጻጸም በቲንክ ታንክ ወይም በጥናትና ምርምር ዘርፍ በሚከናወን ጥናት ውጤታማነቱን የሚያረጋግጥ ይሆናል።

4) የስልጠናው ውጤታማነት የአባላት ከፓርቲው አንጻር ተፈላጊው የባህርይ ለውጥ ማምጣታቸውን፣ የፓርቲውን ተልዕኮ ውጤታማ በሆነ ሁኔታ መሳካቱን፣ ተልዕኮ የመሸከም ፍቃደኝነትና ትጋት፣ በተሰማሩበት የስራ መስኮች ያላቸው አፈጻጸም መሻሻል እንዲሁም መልካም ስነ-ምግባር እየተሸሻለ መሆኑን የሚያካትት ይሆናል።

# ክፍል አራት

# የአባላት ስንብት አፈጻጸም

## 31. በአባሉ ጥያቄ መሰረት ስለሚከናወን ስንብት

1) አንድ አባል በራሱ ፍላጎት ፓርቲውን ለመልቀቅ ወስኖ ሲጠይቅ በእጁ የሚገኙ የፓርቲ ሰነዶችና ንብረቶች በማስረከብ ከአባልነት መልቀቅ ይችላል፡፡

2) ከላይ በንኡስ አንቀጽ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በራሱ ጥያቄ መሰረት ከፓርቲው ለመልቀቅ ያሰበ አባል የሚለቅበትን ምክኒያት በመጥቀስ ለተደራጀበት ህዋስ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

3) ህዋሷ ማመልከቻውን በመቀበል አባሉ የሚለቅበትን ምክኒያት ትመረምራለች፡፡

4) በምርመራው አባሉ አስገዳጅና ከአቅም በላይ በሆነ ምክኒያት የሚለቅ መሆኑ ሲታወቅ አባሉ በቀጣይ፡-

   ሀ) በፓርቲው ደጋፊነት እንዲቀጥል ወይመ፣

   ለ) በክብር አባልነት እንዲቀጥል ወይም፣

   ሐ) ምቹ ሁኔታ ሲፈጠር ተመልሶ አባል እንዲሆን

   መ) ህዋሷ በመምከር የሚለቀውን አባል የማሳመን ስራ በመስራት ከፓርቲው ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የማሳላጥ ስራ የምታከናውን ይሆናል፡፡ ፡፡

5) በምርመራው አባሉ በፍላጎት ማጣት ወይም አሳማኝ ባልሆነ ምክኒያት የሚለቅ መሆኑ ሲታመን፡-

   ሀ) ህዋሷ አባሉን ወደ ፍላጎት ማጣት ያመጣውን ዋና ጉዳይ በማጣራት ለቀጣይ ትምህርት እንዲወሰድበት ታደርጋለች

   ለ) ህዋሷ ስንብቱ ጤናማ በሆነ አግባብ እንዲሆን የማድረግ ስራን በመስራት ስንብቱ እንዲፈጸም ታደርጋላች፡፡

## 32. በፓርቲው ውሳኔ መሰረት የሚከናወን ስንብት

1) በአባሉ የዲሲፕሊን ጉድለትና ጥፋትን ተከትሉ የሚደረግ ስንብት

ሀ) አንድ አባል ባሳየው የዲሲፕሊን ጉድለትና በፈጸመው ጥፋት ምክኒያት የሚደረግ ስንብት

ለ) በፓርቲው አሰራሮች መሰረት ግዴታዎቹን ሳይወጣ ሲቀርና አሰራሮችን ጥሶ ሲገኝ

2) በሌሎች አሰገዳጅ በሆኑ ጉዳዮች ምክኒያት የሚደረግ ስንብት

አንድ አባል፡-

ሀ) እድሜው 65 ሲደርስ፣

ለ) በጤንነት መጓደል እና በሌሎች አስገዳጅ ማህበራዊ ችግሮች ምክኒያት የአባልነት ሙሉ ተሳትፎን ወይም ግዴታዎቹን እየተወጣ መቀጠል ሳይችል ሲቀር፣

ሐ) በፓርቲው አሰራሮች እና በሀገራችን ህጎች መሰረት የፓርቲ አባል ሆኖ መቀጠል በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ መሆኑ ሲረጋገጥ ከፓርቲው አባልነት እንዲለቅና እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡

## 33.<u>ስንብትን ተከትሎ የሚኖር መረጃ አያየዝ</u>

1) በተለያዩ ምክኒያቶች የተከናወኑ ስንብቶች መረጃዎች በየአደረጃቶቹ በአግባቡ ተመዝግበው መያዝና ስራ ላይ መዋል ይኖረባቸዋል

2) በየአደረጃጀቶቹ የተመዘገቡ መረጃዎች በየደረጃው ላሉ ጽህፈት ቤቶች ሪፓርት ተደረገው በፓርቲው ዳታቤዝ ውስጥ ተመዝግበውና ተስተካክለው መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

## 34.<u>ከሙሉ አባልነት ስንብት በኃላ ስለሚኖር የክብር አባልነት</u>

1) አንድ ሙሉ አባል ከሙሉ አባልነቱ በሚከተሉት ምክኒያቶች ወደ ክብር አባልነት ሊሸጋገር ይችላል፡-

ሀ) እድሜው 65 ሲሞላው፣

ለ) በፓርቲው ውስጥ 10 ዓመትና ከዚያ ባላይ አገልግሎ እንደ ህመም ባለ ከአቅም በላይ በሆነ ምክኒያት ሙሉ ተሳትፎ መድረግ ሳይችል ሲቀር፣

ሐ) በፓርቲው ውሳኔ መሰረት፡፡

2) ከላይ በንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ከሙሉ አባልነት ወደ ክብር አባልነት የተሸጋገረ የክብር አባልነት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

3) የክብር አባልነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው አባል የክብር አባል ተብሎ ይጠራል፡፡

4) የክብር አባልነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው አባል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በተለያዩ የፓርቲ መደረኮች በክብር እንግድነት እንዲገኝ ሊደረግ ይችለል፡፡

5) አንድ የክብር አባል ለፓርቲው ጠቃሚ የሆኑ አሰተያየቶችን፣ ምክሮችን እና ሂሶችን በየደረጃው ላሉ የፓርቲ አደረጃጀቶች በጽኁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

6) በየደረጃው ያሉ የፓርቲ አደረጃጀቶች በፓርቲው ውስጥ ረዘም ያለ አገልግሎች የነበራቸውን የክብር አባላት ለፓርቲው አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉበትን ሁኔታ በመለየት ሚናቸውን እንዲወጡ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 35. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት

1) በመመሪያው አፈጻጸም ሂደት ቅሬታ ያለው ዕጩ አባል ወይም ሙሉ አባል ቅሬታውን ዌም አቤቱታውን አሰራርን በጠበቀ መለኩ ለሚመለከተው የፓርቲ መዋቅር ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ቅሬታ የቀረበለት የፓርቲ አካል በፓርቲው የዲሲፕሊን መመሪያ መሠረት ቅሬታውን የማስተናገድ ግዴታ አለበት፤
3) ቅሬታ አቅራቢው በፓርቲ መዋቅር በተሰጠው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ በየደረጃው ለሚገኙ የፓርቲ የኢንስፔክሽን እና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4) አቤቱታ የቀረበለት የኢንስፔክሽንና የሥነ ምግባር ኮሚሽን መዋቅር የአቤቱታ አቅራቢውን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔውን ለአቤቱታ አቅራቢውና ውሳኔ ለሰጠው አካል በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

### 36.መመሪያውን ስለማስፈጸም

ይህ መመሪያ በየደረጃው ያሉ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና አደረጃጀቶች በተሟላ ሁኔታ መፈፀምና ማስፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡

### 37.ስለተጠያቂነት

1) በዚህ መመሪያ ውስጥ ከተደነገገው አሰራር ውጭ አባልን መመልመልም ሆነ ማሰናበት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፣

2) የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት የተላለፈ ማንኛውም አመራር ወይም አካል ወይም አባል በፓርቲው የዲሲፕሊን መመሪያ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

## 38. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው አሰራሮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ልማዳዊ አሰራሮች ወይም መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

## 39. መመሪያውን ስለማሻሻል፣

ይህን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ሊያሻሽል ይችላል።

## 40. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ከጸደቀበት **ጥቅምት**_______ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ፣ ጥቅምት ----- ቀን 2017 ዓ.ም**

**ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የብልጽግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት**